# የወያኔን ድቅድቅ ጨለማ ላብ አደሩ በትግል ችቦ ያበራዋል!

## ሜይ ዴይን በማስመልከት በስደት ከምንገኝ የቀድሞ የኢትዮጵያ ሰራተኛ ማሕበራት መሪዎች የተሰጠ መግለጫ

የዓለም ሰርቶ አደሮች የትግላቸው ፣ የመስዋዕትነታቸው እና የድላቸው መታሰቢያ የሆነው ሜይ ዴይ እነሆ ዘንድሮም የሚከበረው ላብ አደሩ መደባዊ ብቻ ሳይሆን ሰብዓዊ እና ብሄራዊ መብቱ ጭምር በአምባገነኖች ጫማ ስር በተረገጠበትና የኑሮ ውድነቱ ተባብሶ  የሰርቶ አደሩ ቤተሰብ በችግር እና በችጋር በሚገረፍበት አሳዛኝ ሁኔታ ሥር ነው።

የኢትዮጵያ ላብ አደር  ከአራት አሥርት ዓመታት በፊት በእነ አበራ ገሙ መሪነት የጀመረውን የነጻ እና ጠንካራ ብሄራዊ የሰራተኛ ማኅበር የማቋቋም ራዕይ እንዳነገበ ፣ ይህንኑ ራዕይ ዕውን ለማድረግ የየዘመኑን አምባ ገነኖች እንደተፋለመ እና  መስዋዕትነት እንደከፈለ ይገኛል።

እነ አበራ ገሙ የአጼ ኃይለ ሥላሴን ዘውዳዊ ሥርዓት ተጋፍጠው እና ተፋልመው የሰራተኛ ህግ ያልነበራት ሃገራችን የሰራተኛ ህግ እንዲኖራት አድርገዋል። መረን ተለቆ የነበረውን የስርዓቱን እና የአሰሪዎችን ግፍ ግን የህግ ገደብ አላቆመውም። የተበታተነውን እና በእድር እና ዕቁብ ደረጃ በኅቡዕ ሲካሄድ የነበረውን የሰራተኛ ትግል አስተባብረው በሃገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ  ሃገር አቀፍ ብሄራዊ ማኅበርን እውን በማድረግ ማኅበራቸውን የኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማኅበርን  (ኢሰአማን) በትግላቸው መስርተዋል።

በትግል ህልውናውን የተቀዳጀው ኢሰአማ  ግን በነፃነት እንዲሰራ በአፄው ሥርዓት  አልተፈቀደለትም። የላብ አደሩን የመብት ጥያቄ አንስቶ ለመንቀሳቀስ አሁዱ ብሎ ሲነሳ በአፄው ሥርዓት እና በውስጥ ቅጥረኞቻቸው በግፍ ተዘምቶበት የማኅበሩ መሪ የነበረው አቶ አብረሃም መኮንን የማኅበር መሪነቱን ተገፍቶ እንዲለቅ ተደርጎ «ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው ለቀቁ» ተባለ። ጀግናው የኢትዮጵያ ሠራተኞች የትግል አባት አቶ አበራ ገሙ በግፍ ተገድሎ «ህይወታቸውን በገዛ እጃቸው አጠፉ» ተባለ።  አበራ ገሙ ግን፣ እሱ ሞቶ የማይሞተውን የትግል ቀንዲል ተክሎ አለፈ። ሜይ ዴይ የላብ አደሩ የትግል መዘክር ቀን ነውና የላብ አደሩን የትግል ፈር ቀዳጆች እነ አበራ ገሙን በሜይ ዴይ መዘከር ተገቢ ነው።

የነ አበራ ገሙን ደም በግፍ አፍስሶ ማኅበራቸውን በተላላኪዎቹ ቁጥጥር ስር ያስገባው የአፄው ሥርዓት በሕዝባዊ ትግል ተደምስሶ  ወደ ታሪክ ትብያ ሲጣል የሕዝቡን ትግል በጠብ መንጃ ጠልፎ ሥልጣን ላይ የወጣው ወታደራዊ ደርግ በተራው ፋሽስታዊ በትሩን በላብ አደሩ ላይ ለመሰንዘር  ተሰለፈ። አፈናው ከምንጊዜውም የከፋ ሆነ።  መብቱን የጠየቀ ሁሉ በጅምላ ተጨፈጨፈ።  የላብ አደሩም ደም ከመስሪያ ቤቱ ደጃፍ  እስከ አደባባይ ተንዠቀዠቀ።  የዘጠኝ ወር ነብሰ ጡሩዋን ወይዘሮ ዳሮ ነጋሽን ሆዱዋ ውስጥ ከሚላወሰው ሕፃን ጭምር በማረድ ደርግ አረመኔአዊ ጭፍጨፋውን አጠናክሮ ቀጠለበት። የላብ አደሩ የነጻ ማኅበር ህልም  በደርግ የመኢሰማ ቅዠት ተተክቶ ላብ አደሩ በመረጣቸው መሪዎች ሳይሆን በደርግ ሹመኞች ሲረገጥ፣ ሲዋረድ ፣ እንደ መንጋ እየተነዳ ገዳዮቹን እንዲያወድስ  ሲገደድ ፣ ለጦርነት ሲማገድ ኖሮአል።  ሜይ ዴይ የላብ አደሩ የትግል መዘክር ቀን ነውና የዘጠኝ ወር ነብሰ ጡሩዋን ወይዘሮ ዳሮ ነጋሽን እና እንደሱዋው መሪር መስዋዕትነት ከፍለው ያለፉ ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ ላብ አደሮችን እና የላብ አደር መሪዎችን በሜይ ዴይ መዘከር ተገቢ ነው።

አረመኔአዊው የደርግ ሥርዓት በሕዝባችን ያላሰለሰ ትግል ተዳክሞ እና በዓለም አቀፍ የግፍ አጋሮቹ ተተፍቶ በተራው ወደ ታሪክ ትብያ ሲጣል አሁንም የሕዝቡን ድል በጠመንጃ የነጠቀ ዘረኛ እና ጎሰኛ የሕወሀት ሻዕቢያ ጥምር ቡድን ወደ ሥልጣን በመምጣቱ የግፉ ዘመን በአዲሶቹ ግፈኞች ተራዝሞ ቀጠለ። የላብ አደሩን አምባ ገነን መንግሥት ለመመሥረት እታገላለሁ ሲል የነበረው የሕወሀት ማሌሊት ጎሰኛ ቡድን በሥሙ ሲምልበት እና ሲገዘትበት የነበረው ላብ አደር ላይ አምባገነናዊ የግፍ በትሩን የሰነዘረው ገና የመንግሥት ሥልጣን በጉልበት እንደተቆጣጠረ ነው።  የደርጉ ኢሰማ መቀመጫ የነበረውንና የኢትዮጵያ ላብ አደር አንጡራ ሀብት የሆነውን ብሔራዊ ጽ/ቤቱን  የወያኔ ሰራዊት አሰፈረበት። የኢትዮጵያ ላብ አደር አንጡራ ሀብት የነበሩትን ብሔራዊ ጽ/ቤቱን ጨምሮ በመላው ሃገሪቱ የነበሩ የማህበሩ ሕንጻዎችን ፣ ተሽከርካሪዎችን፣ የገቢ ማስገኛ ተቋማትና ፣ ጥሬ ገንዘብ ጭምር በመውረስ  ፀረ ላብ አደር ዘመቻውን ተያያዘው።

በወያኔ አምሳል የተቀርጸ እና በማሌሊት ሳንባ የሚተነፍስ ተለጣፊ የሠራተኛ ማህበር ለማቋቋም አደራጅ ኮሚሽን የተባለ እና ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ ይዘወር የነበረ አካል ሕወሃት ፈበረከ። ነገር ግን በፈበረከው ኮሚሽን አማካይነት የኢትዮጵያ ሠራተኞችን በዘርና በቋንቋ አደራጅቶ የሕወሀት የጎሳ ግርግር አድማቂዎች ለማድረግ፣ የሕወሃት ምልምል ካድሬዎችንም በምርጫ ሥም በሰራተኛው ላይ ለመሾምና ላብ አደሩን በማሌሊት ሳንባ ለማስተንፈስ የተቀነባበረው ሴራ በላብ አደሩ ቆራጥ ትግል ሙሉ በሙሉ ተጋልጦ በመተፋቱ በዘር የማደራጀት ሕልሙም ሆነ ማኅበርሩን በሕወሀት ቁጥጥር ሥር ለማስገባት የነበረው ዕቅድ ሙሉ በሙሉ ከሽፎበታል።   ማሌሊት በአደራጅ ኮሚሽን አማካይነት ገምዶ አንገቱ ላይ ሊያስገባለት የነበረውን የግፍ ሸምቀቆ ላብ አደሩ በትግሉ በጣጥሶ ነጻውን የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማሕበራት ኮንፌዴሬሽን  (ኢሠማኮ)ን በማቋቋም የነፃ እራሱን የቻለ እና የጠንካራ ማሕበር ባለቤት ለመሆን ያለውን የትግል ብቃት እና ቁርጠኝነት አስመሰከረ።

አምባ ገነኖች የነፃነት ጠላቶች ናቸውና ነፃ አመለካከት፣  ነፃ ማኅበር ፣ ነፃ አካሄድ፣ ነፃ ፍርድ ቤት፣  ነፃ ፕሬስ በአጠቃላይ ከነጻነት ጋር የተቆራኘን ነገር በሙሉ ይፈራሉ። ስለሚፈሩትም ለማጥፋት ያለ የሌለ የግፍ በትራቸውን አንስተው ይሰነዝራሉ። ሥልጣናቸው ያለ ግፍና ዕመቃ ዕድሜ እንደሌለው ስለሚያውቁ በሥልጣን ለመቆየት የማይፈጽሙት ግፍ የለም።

ላብ አደሩ የሕወሃት ማሌሊትን የግፍ ሠንሠለት በትግሉ በጣጥሶ ነፃውን ኢሰማኮን ቢመሰርትም ወያኔ ሽንፈቱን ተቀብሎ የሠራተኛውን ውሳኔ ለማክበር አምባገነናዊ ተፈጥሮው አይፈቅድለትም እና በመድረክ የተጎነጨውን ሽንፈት  ለመቀልበስ በጦር ኃይል ጭምር ኢሰማኮ ላይ ዘመተ።

የሃገራችን አምባገነኖች በሙሉ በላብ አደሩ ላይ ጦርነት ሲያውጁ ከላብ አደሩ መሃል የሚወጡ፣  ህሊናቸውን ለጥቅም የሸጡ፣ የውስጥ ከሃዲዎችና  ግብረ በላዎችን ትብብር አጥተው አያውቁም።  በዘመነ ወያኔ ኢሰማኮን ከውስጥ የወጉትን ከሃዲዎች ግን ልዩና እጅግ አሳፋሪ የሚያደርጋቸው «በሥልጣን ላይ የወጣው የሕወሃት ሻዕቢያ ጥምረት የኛ ዘር ስለሆነ ዘመኑ የኛ ነውና እንጠቀማለን» በሚል ዘረኝነትን እና የደም ቆጠራን ከህሊና ቢስ ስግብግብነት ጋር ባጣመረ ቅኝት ላይ የተመሰረቱና በደም የተሰባሰቡ መሆናቸው ነው። እነዚህን የሕወሃት ሻዕቢያ ጥምር ቡድን አባላት ልዩ የሚያደርጋቸው በከቡሩ የኢትዮጵያ ላብ አደር ጠቅላይ ምክር ቤት ሥብሰባ ውስጥ ሕወሃት ያስታጠቃቸውን የጦር መሳሪያ ይዘው ገብተው የላብ አደሩ መሪዎች ላይ በመደገን ለማስፈራራት መሞከራቸው ነው። የኢሰማኮን የትግል ታሪክ በዘከርን ቁጥር ይህን አሳፋሪ፣ ዘረኛ እና ወራዳ የክህደት ተግባር ታሪክ እንዳይረሳው ማድረግም ተገቢ ነው።

በአንፃሩ የኢሠማኮ ጠቅላይ ምክር ቤት ከውስጥ በሕወሃት ሻዕቢያ ጀሌዎች፣ ከውጭ በሙሉ መንግሥታዊ የጦር ኃይል ፣ ፖሊስና ደህንነት ማስፈራራት፣ ወከባና ዕመቃ ሳይበገር ላብ አደሩ የጣለበትን አደራ ያለማወላወል በመጠበቅ ባካሄደው አኩሪ ትግል ታሪኩን ከነ አበራ ገሙ እና ከነ ዳሮ ነጋሽ ጎን በወርቅ ቀለም ፅፏል። በዚህ ቆራጥ ትግል ውስጥ የተሳተፉ የኢሠማኮ ጠቅላይ ምክር ቤት አባላት፣ የጠቅላላ ጉባዔ አባላት፣ እና የትግሉ አጋር የነበሩ ጀግና ላብ አደሮች ከስራ መባረርን፣ እስርን፣ ስደትንና ሞትን ተቀብለዋል። ሜይ ዴይ የላብ አደሩ የትግል መዘከር ቀን ነውና የኢሰማኮ የጠቅላላ ጉባዔ አባላትን፣ የጠቅላይ ምክር ቤት አባላትን እና ከኢሰማኮ ጎን ቆመው የወያኔን ግፍ በጽናት የታገሉ ሃቀኛ ላብ አደሮችንና መሪዎችቻቸውን በሜይ ዴይ መዘከር ተገቢ ነው።

ለዓመታት በዘለቀ ዕመቃና በጦር ኃይል ጭምር ታግዞ የሠራተኛ መሪዎችን ያሳደደ እና የኢሠማኮን ግቢ በኃይል የተቆጣጠረው ወያኔ ዛሬም በሃገሪቱ ነፃ ማሕበር ያለ ለማስመሰል ቲያትሩን በሃገር ውስጥ እና በውጭ ቀጥሎበታል። በላብ አደሩ ግቢ በወያኔ የተሾሙት ካድሬዎች ዓለም አቀፍ መሥፈርቶችን ያላሟላ የሠራተኛ ሕግ ከወያኔ ጋር አርቅቀው በሰራተኛው ላይ ጭነዋል። በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ ላብ አደሮች ከሥራ ሲባረሩ ከወያኔ ጋር ተባብረዋል። ሕወሀት በሀቀኛ የላብ አደር መሪዎች ትግል በዓለም የስራ ድርጅት አይ ኤል ኦ መድረክ ሲከሰስና ሲፈረድበት ከወያኔ ጎን ቆመው ለወያኔ ተሟግተዋል። የሕወሃት ወያኔን የግንቦት 1997 ምርጫ ለማድመቅ «የምርጫው ጉዳይ ያገባናልና ሕዝብ እና ሠራተኛውን እናወያያለን» በማለት ያዙን ልቀቁን ሲሉ እንዳልነበር ወያኔ የሕዝብን ድምፅ በአደባባይ ሲዘርፍና ድምፄ ይከበር ብሎ በሰልፍ የወጣውን ሕዝብ ሕጻን፣ ሽማግሌ፣ ሴት፣ ወንድ ሳይል በግፍ ሲጨፈጨፍ ትንፍሽ የሚሉበት ወኔ አላገኙም። የወያኔን የምርጫ ቲያትር ለማጀብ «የዴሞክራሲያዊ ምርጫ ጥያቄ የላብ አደሩም ጥያቄ ነው» እንዳላሉ ሕዝባችን በዴሞክራሲያዊ መንገድ በምርጫው ያረጋገጠውን ነጻነቱን በወያኔ የግፍ ጭፍጨፋ ሲነጠቅ ሕጻናት በቀዬአቸው በአጋዚ ጦር ሲመተሩ ፣ እናት በልጆቿ ፊት፣ ልጅ በናቱ ፊት፣ ሚስት በባል ፊት፣ ባል በሚስት ፊት እየተረሸኑ በሺዎች የሚቆጠሩ ንጹሀን ዜጎች ውድ ሕይወታቸውን ሲነጠቁ፣ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ በየበረሃው ሲጋዙና ሲታሰሩ ፣ የወያኔ ሹመኛ የሆኑት የላብ አደሩ ግቢ ቅምጥሎች ከላብ አደሩ አንጡራ ሃብት ላይ የሚከፈላቸውን ደሞዝ እየበሉ የወያኔ የግፍ ተባባሪ መሆናቸውን ቀጥለውበታል። ላብ አደሩ እራሱ በመናኛ ደሞዝ ከእጅ ወደ አፍ የማይደርስ ኑሮ እየኖረ ለኢሰማኮ መሪዎች ቱባ ደሞዝ ለመክፈል ሲወስን መሪዎቹን «ይህን ትልቅ ደሞዝ የምንከፍላችሁ በገንዘብ እንዳትሸጡን ነውና አደራ» ብሎ ነበር እነዚህን የክህደት ፊታውራሪዎች ግን ይህ አደራ አላቆማቸውም ከደሃው ላብ አደር አንጡራ ሃብት ላይ የሚከፈላቸውን ቱባ ደሞዝ እየበሉ በአደባባይ የሥርዓቱ ተቀጽላ መሆናቸውን እያወጁ ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ ላብ አደር እነዚህ የወያኔ ቅጥረኞች እና ግብረ በላዎች ፋይዳ ያለው መደባዊም ሆነ ሃገራዊ ጥቅም የማስጠበቅ ተግባር ይፈጽማሉ ብሎ አይጠብቅም። በሜይ ዴይ የላብ አደሩን አደራ ለጥቅም የሸጡ ከሃዲዎችን ማጋለጥም የተገባ ነው። የኢትዮጵያ ላብ አደሮች ታሪክም እነዚህን ከሃዲዎች ተገቢ ቦታቸውን አይነፍጋቸውም።

በወያኔ የተቀነቀነው ነጻ ገበያ የሰራተኛውን ህይወት ሲያመሳቅል እነሆ የወያኔን ዕድሜ አስቆጥሯል። በመዋቅር ማስተካከያ ሥም በፖለቲካ ወገንተኝነትና በዘር ላይ ባተኮረ ዘመቻ በብዙ አስር ሺዎች የሚቆጠሩ ላብ አደሮችን ከሥራ ገበታቸው አፈናቅሎ ጎዳና በመበተን ቤተሰባቸውን በረሃብ አለንጋ ገርፏል። የሸቀጦችን ዋጋ አንሮ የኑሮ ውድነቱን ጣራ አድርሶታል። ይህ ያልተገራ የነጻ ገበያ ዛሬ የአንድ ብር ጨው አስር ብር ሲያስገባ በግንቦቱ ምርጫ በሕዝብ መተፋቱ በማያሻማ ሁኔታ የተረጋገጠለት ወያኔ የሥልጣን ዕድሜውን የሚያሳጥር ሕዝባዊ ተቃውሞን እንዳይቀሰቅስበት በመፍራት የዕውር ድንብሩን ተነስቶ ነጋዴዎች ላይ ጦርነት አውጇል። ችግሩ ከሥርዓቱ እንጂ ከነጋዴው አይደለም። ልቅ እና ያልተገራ የገበያ ሥርዓት ውጤቱ ከዚህ የጨው ትርዒት ሊያልፍ አይችልም። የነጻ ገበያው ሥርዓት በደሃው ሕዝብ ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽዕኖ ፍንትው ብሎ በሚታይበት በዚህ ዘመንም ወያኔ ለነጻ ገበያ ያለውን ታማኝነት ለማሳየት መኀናበሱን ቀጥሎበታል። የደሃውን ሕዝብ ጥቅምና መብት በሕግ ለማስጠበቅና ከልቅና ያልተገራ የነፃ ገበያ ደፈቃ ለመከላከል ፈቃደኝነት እና ቁርጠኝነት ያለው ወገን ማየት እየናፈቀን ነው።

ሃገሪቱ ያለችበትን ሁኔታ ዙሪያ ገባውን ብናየው ጨለማው ሲጠናከር እንጂ የተስፋ ጭላንጭል ሲበራ አይታይም። በግንቦቱ ምርጫ ሕዝባችን ያገኘው ድል በታንክ የተደፈጠጠበት፣ ንፁሃን በግፍ ታርደው ገዳዮቻቸው በነፃነት የሚፎልሉበት፣ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች፣ ስብሰባና ሰላማዊ ሰልፍ የታገደበት፣ ነፃ ጋዜጣ ልሳኑን የተዘጋበት፣ ተቃዋሚዎች በወያኔና በባዕዳን የውስጥ ቅጥረኞች እና የሥልጣን ጥመኞች የሚታመሱበት ፣ የኑሮ ውድነቱ ጣራ የነካበትና ቀኑን ሙሉ በስራ ተጠምዶ የዋለ ሠራተኛ በቀን አንዴ እንኳን እህል መቅመስ ያልቻለበት፣ ሕዝባችን ተራብኩ ሲልና የዳቦ ጥያቄ ሲያነሳ ወያኔ የልጅ ልጆቻችንና የነሱ ልጆች ጭምር የማይከፍሉት ብድር እየተቀበለ ስለሰራው አስፋልት እና ስለ ጥቂት ሃብታሞች ሕንፃ መሥራት እያወራ የሚያሾፍበት፣ የሃገሪቱ ወጣት ምንም አይነት የሥራ እድል እና ተስፋ የተነፈገበት፣ ከላይ እስከታች ያለው መንግሥታዊ መዋቅር ያለ ጉቦ የማይሰራበት፣ መሠረታዊ የጤናና የትምህርት አገልግሎቶች ደረጃቸው አዘቅት የወረደብት ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ነው ያለነው።

ወያኔ የሲቪል ማሕበረሰቡን በቁጥጥሩ ሥር ለማስገባት ለአመታት ባካሄደው አረመኔያዊ ዕመቃ አሉ የሚባሉትን ጠንካራ ማሕበራት በሙሉ ተራ በተራ አጥፍቶ በራሱ አሻንጉሊቶች ለመተካት ፀረ ሲቪክ ማሕበራት ዘመቻውን ገፍቶበታል። ነጻውን የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማሕበራት ኮንፌዴሬሽን ኢሠማኮን በወታደራዊ ወረራ ተቆጣጥሮ መሪዎቹን በሃገር ውስጥና ከሃገር ዉጭ አሳዶ ካድሬዎቹን በኢሠማኮ ግቢ ኮልኩሎዋል። አንጋፋውን የኢትዮጵያ መምህራን ማሕበር ኢመማን ጠንካራ መሪዎቹን አስሮ፣ ገድሎ፣ አሳዶ እና በፍርድ ቤት ሥም በሚንቀሳቀሱ ካድሬዎቹ ጭምር ተጭኖ መምህሩ ያልመረጣቸውን ካድሬዎች ለመሾም አሰፍስፏል። የኢትዮጵያ ነፃ ጋዜጠኞችንም እንዲሁ አስሮ፣ ገድሎ፣ አሳዶ መሪዎቹ እና አባሎቹ በስደት ሃገር እንዲንቀሳቀሱ አስገዲዷቸዋል። የሲቪክ ማህበረሰቡን ነጻነት ከአምባ ገነኖች ጫማ ሥር ለማውጣት ወደር የለሽ መስዋዕትነት የከፈሉትንና የትግል አጋሮቻችን የሆኑትን እነዚህን ሲቪክ ማሕበራት በሜይ ዴይ መዘከር ተገቢ ነው።

ወያኔ የዴሞክራሲ መሠረት የሆኑትን የሲቪክ ማሕበራት እንዲህ እያፈራረሰ እና እየናደ «ዴሞክራሲን እየገነባሁ ነው» የሚለውን ቧልት ቀጥሎበታል። በሃገራችን ነፃ የሲቪክ ማሕበራት ያሉበት ሁኔታ የወያኔን ፀረ ዴሞክራሲያዊነትና አፋኝነት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ማስረጃ ነው። የወያኔን አምባገነናዊ እና ፋሽስታዊ አገዛዝ ለማንበከርክ እና የሕዝባችንን ነጻነት ለማረጋገጥ በሚካሄደ ሕዝባዊ ትግል ተሰባስበን በጋራ እንድንታገል ለኢትዮጵያ ሲቪክ ማሕበራት የዓለም ሰርቶ አደሮች የትግል አጋርነት ቀን በሆነው ሜይ ዴይ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በአምባገነናዊ እና ፋሽስታዊ እመቃ ሥር እየተረገጠ እና እየተጨፈጨፈ ለሠራተኛው ሕዝብ የዴሞክራሲ ደሴት መገንባት አይቻልም። በመሆኑም ወያኔ በሕዝባችን ላይ የጫነውን ድቅድቅ ጨለማ በትግል ችቦ ለማብራት ሠራተኛው ሕዝብ በግንቦት 1997 ምርጫ እንዳደረገው ሁሉ ዛሬም ከንዱን ከፀረ ወያኔ ታጋይ ኃይሎች ጋር ማንሳትና ከጎናቸው ቆሞ ሁለንተናዊ ድጋፍ መስጠትና በትግሉ ሙሉ በሙሉ መሳተፍ የነፃነት ብቸኛው መንገድ መሆኑን አምኖ መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል።

ነፃነት ምንጊዜም የትግል እና የመስዋዕትነት ውጤት ነው !
ሚያዚያ 2000 ዓ/ም